# ህብረትና ዘመን

አብርሃም በየነ

የዕምነት ቃሉን ሰጥቶ እሳት ለገባ
አህያም ለጅብ ሹም ሆኖ ጃንደረባ
ሲሆን የአንገት ማተብ ክህደት ላመኔታ
እየሳቁ ማልቀስ እያነቡ እስክስታ. . .
እነዚህ ክስተቶች ባይተዋር ለህዝቡ
ህብረ-ቀለም ፈጥረው ሲኖሩ ባግባቡ
የማይሆነው ሆኖ ታይቶት በምናቡ
ላም አለኝ በሰማይ . . . በሚመስል ተስፋው
ስንቱን አዲስ ዓመት እያስረጀ ገፋው።
ታህሳስ 2007

ለሁላችሁም መልካም አዲስ ዓመት